# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር ደብዲ/001/2016

**ቀን፡ ሰኔ 27/2016**

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለማይ ሹዝ ኤንድ ሌዘር ኘሮዳክትስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለሰጠው የብድር ገንዘብ በመያዣነት (ዋስትና) የያዛቸውና በደ/ብርሃን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ማሽነሪዎችን (ንብረቶችን) ከኮሌጁ ቅጥር ግቢ ወደ ኘሮጀክቱ ሳይት (ዳሸን አካባቢ ወደሚገኘው የድርጅቱ መጋዘን) የማጓጓዝ ስራ የሚሰራን ድርጅት (ግለሰብ) አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም ሥራውን መስራት የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሣሪያ፣ የሥራ አመራር ችሎታ እና የሰው ኃይል ያለው እንዲሁም አስፈላጊ ህጋዊ ዶክሜንቶችን የሚያሟላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የጨረታ ሰነዱን በመውሰድና በመሙላት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ተከታታይ 10 የሥራ ቀናት ውስጥ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደ/ብርሃን ዲስትሪክት (ፃድቃኔ ህንፃ 1ኛ ፎቅ) በሚገኘውና ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በማስገባት መጫረት የሚቻል መሆኑን እንገልፃለን ፡፡

ማሳሰቢያ፡-

- ተጫራቾች የሚጫነውን ዕቃ እና የሚጓጓዝበትን ቦታ ማየት ከፈለጉ በባንኩ በደ/ብርሃን ዲስትሪክት ቢሮ (ፃድቃኔ ህንፃ 1ኛ ፎቅ) በመምጣት ፕሮግራም ማስያዝ ይችላሉ፡፡
- ተጨራቾች ዝርዝር መረጃ የያዘውን የጨረታ ሠነዱን ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደ/ብርሃን ቅርንጫፍ ማግኘት ይችላሉ፡፡
- የጨረታ ሳጥኑ የሚከፈተው ከጨረታ ማለቂያው ቀን ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ ይሆናል፡፡

ለበለጠ መረጃ፡- ስ.ቁ 011-637-58-51

**የኢትዮጵያ ልማት ባንክ**

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
# ደብረ ብርሃን ዲስትሪክት
# የግልጽ ጨረታ ሰነድ

**የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር ደብዲ/001/2016**

**ጨረታው የወጣበት ቀን ሰኔ 27/2016 ዓ.ም**

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደብረ ብርሃን ዲስትሪክት ባንኩ ለማይ ሹዝ ኤንድ ሌዘር ፕሮዳክትስ ኃ/የተ/የግ/ማ ለሰጠው የብድር ገንዘብ በመያዣነት (ዋስትና) የያዛቸውና በደ/ብርሃን ፖ/ቴክኒክ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ማሽሪዎችን (ንብረቶችን) ከኮሌጁ ቅጥር ግቢ ወደ ፕሮጀክቱ ሳይት (ደ/ብርሃን ዳሸን አከባቢ) ለመጫን፣ ለማጓጓዝ፣ ለማውረድ፣ ለመደርደርና በስርዓት ለማስቀመጥ የፈለገ ሲሆን ይህንኑ ስራ በጨረታ አወዳድሮ ስራ ማሰራት ይፈልጋል፡፡

**1.የተወዳዳሪዎች መስፈርት**

**ተወዳዳሪዎች የሚከተለውን መስፈርት ማሟላት አለባቸው፡-**

1.1. አግባብነት ያለው የታደሰ ንግድ ፈቃድ ፣

1.2. የግብርና የታክስ ግዴታውን የተወጣ፣

1.3. በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፍ ታግዶ ከሆነ የእገዳ ጊዜውን ያጠናቀቀ፣

1.4. በሚገቡት ስምምነት መሰረት ለመፈጸም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሳሪያ፣ በሚሰራዉ ስራ የስራ አመራር ችሎታ፣መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ያለው እንዲሁም ባንኩ የሚሰጠውን የአሰራር መመሪያ የሚከተል፣

1.5. በጨረታው የሚሳተፈው የውጭ አገር ድርጅት ከሆነ የኩባንያ ምዝገባ የምስክር ወረቀትና ፈቃድ ማቅረብ ይኖርበታል፣

1.6. በዋጋ ማቅረቢያው ሰንጠረዥ ላይ ስርዝ ድልዝ መኖር የለበትም፣

1.7. ዋጋ ሰጪው የድርጅቱን ማህተም እንዲሁም ፊርማ እና የድርጅቱን አድራሻ ማድረግ አለበት፣

Development Bank of Ethiopia Debre Birhan District

1.8. የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ግዴታውን እንዲሁም ሌሎች በዘርፉ ያለውን ልምድ የሚያስረዱ ሰነዶችን /የምስክር ወረቀት ማያያዝ ይኖርበታል፣

1.9. ከዚህ በፊት በሙያው ልምድ የሌለው በዉድድሩ እንዲሳተፍ አይፈቀድም።

1.10. ሰነዱን በታሸገ ፖስታ በማድረግ ማቅረብ ይኖርበታል፣

1.11. ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያውን /የጨረታ ሰነዱን/ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደብረ ብርሃን ቅርንጫፍ ማግኘት ይችላሉ።

1.12. ሰነዱን በመሙላት ሰነዱን ይህ ጨረታ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደብረ ብርሃን ዲስትሪክት (ፃድቃኔ ህንፃ 1ኛ ፎቅ) በሚገኘውና ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

1.13. ከላይ ከተጠቀሰው ቀን በኃላ የሚቀርብ የዋጋ ማቅረቢያ /የጨረታ/ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፣

1.14. ጨረታው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደብረ ብርሃን ዲስትሪክት የጨረታ ቀን ማለቂያው ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ይከፈታል፣

1.15. ተወዳዳሪው ለጨረታ ማስከበሪያ ያቀረበውን ዋጋ *10% በሲፒኦ ወይም በባንክ ዋስትና ማስያዝ የሚኖርበት* ሲሆን ለተሸናፊዎች መሸነፋቸው እንደታወቀ ወዲያውኑ የሚመለስ ሲሆን ለአሸናፊው ለአፈጻጸም ዋስትና ሆኖ የሚቆይ ሲሆን ስራውን ባጠናቀቀ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ይለቀቅለታል፣

1.16. ጨረታው ከተከፈተ በኂላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግ እንዲሁም ከጨረታው ራስን ማግለል አይቻልም፣

1.17. ባንኩ ጨረታውን የመሰረዝ መብት አለው፣

2. *አጠቃላይ ግዴታዎች፡-*

2.1. ማሽነሪዎች በሚጓጓዙበት ጊዜ ጉዳት እንዳይደርስባቸው መታሸግ፣ በፓሌት ላይ ማስቀመጥ (Palletized) እንዲሁም እንዳይንቀሳቀሱ አድርጎ ማሰር፣

2.2. ማሽነሪዎችን በአግባቡ አሽጎ ማጓጓዝ፣

2.3. ማሽነሪውን በራሱ የሚጭን እና የሚያወርድ፣

2.4. ተጫራቹ የጨረታው ጊዜ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ራሱን ከጨረታ ካገለለ ያስያዘው ገንዘብ ለባንኩ ገቢ ይደረጋል፣

2.5. ተጫራቹ በጨረታው አሸናፊ መሆኑ ተገልጾለት ስራውን በገባው ቃል መሰረት ማከናወን ካልቻለ ያስያዘው ገንዘብ ለባንኩ ገቢ ይሆናል፣

2.6. ባንኩ ስራው ተሰርቶ በተጠናቀቀበት አምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ክፍያ ይፈጽማል፣

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደብረ ብርሃን ዲስትሪክት Development Bank of Ethiopia Debre Birhan District

2.7. አሸናፊው ስራውን ለሚያዘገይበት ለእያንዳንዱ ቀን በዋጋው 1/1000ኛ ቅጣት ለባንኩ የሚከፍል ሲሆን ጠቅላላ ቅጣቱ ከ10% በላይ መሆን የለበትም፣

2.8. ከላይ በተ.ቁ 2.8 ያለው ቢኖርም ባንኩ ቅጣቱ 10% መሙላቱን ሳይጠብቅ የአምስት ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስምምነቱን ያቋርጣል፣ ለውል ማስፈጸሚያ የያዘውን 10% ዋስትና ይወስዳል፣ ዋስትናው ካልሸፈነውም ለደረሰበት ጉዳት ተጨማሪ ክፍያ ይጠይቃል፣

2.9. አሸናፊው ማሽኑን በጥንቃቄ እና በአግባቡ ጉዳት ሳይደርስበት የመጫንና ባንኩ ወደ አዘጋጀው ማስቀመጫ ቦታ በጥንቃቄ ምንም አይነት ጉዳት እንዳይደርስ በማድረግ የማድረስና ወደ ማስቀመጫው የማስገባት ኃላፊነት አለበት፣

2.10. በሚጫንበት ወቅት፣ በማጓጓዝ ወይም ማሽኑን ሲያወርዱ በማሽኑ ላይ ለሚፈጠር ጉዳት ወይም ብልሽት አሸናፊው ኃላፊነት አለበት፣

2.11. አሸናፊው ስራውን ከላይ በተገለጸው አግባብ የመስራት ግዴታ ያለበት ሲሆን በዚሁ አግባብ ካልፈጸመ ባንኩ ውሉን የማፍረስና ለውል ማስፈጸሚያነት የተያዘውን ገንዘብ የመውሰድና ለደረሰበት ተጨማሪ ጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት አለው፣

3. <u>የሚጓጓዙ ማሽነሪዎች ዝርዝር</u>፡-

3.1. ከታች የተዘረዘሩት ማሽነሪዎች ከኮሌጁ ቅጥር ግቢ ወደ ፕሮጀክቱ ሳይት የሚጫኑ፣ የሚጓጓዙ፣ የሚወርዱና በሥርዓት የሚቀመጡ ናቸው፡፡

| ተ/ቁ | የንብረቶች ዝርዝር | ብዛት | የሚገኙበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | TPR compound granular producing plant (with extruder, mixer, die cutter and conveyer) | line | ደ/ብርሃን ፖሊ. ቴክኒክና ሞያ ኮሌጅ | |
| 2 | TPR shoe outsole injection molding | 04 | | |
| 3 | PVC outsole injection machine | 03 | | |
| 4 | Cooling (molding chiller) | 01 | | |
| 5 | Waste plastic crusher | 01 | | |
| 6 | Travelling head die cutting presses | 01 | | |

Development Bank of Ethiopia
Debre Birhan District

| የድርጅቱ/ግለሰብ ስም | ስራውን ለመስራት የቀረበው ዋጋ/VAT/TOTን ጨምሮ/ | ስራው ተሰርቶ የሚጠናቀቅበት ጊዜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| | | | |

*ማስታወሻ፡-*

- ተጫራቾች የሚጫነውን እቃ እና የሚጓጓዝበትን ቦታ ማየት ከፈለጉ በባንኩ በደ/ብርሃን ዲስትሪክት ቢሮ /ዓድቃኔ ህንፃ 1ኛ ፎቅ/ በመምጣት ፕሮግራም ማስያዝ ይችላሉ፡፡

ለበለጠ መረጃ፤

ስልክ ቁጥር፡-01 16 37 58 51